# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 251 የካቲት 28 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለወያኔ የ"ከፋፍለህ በየተራ ቀጥቀጥ" ፖሊሲ መድሃኒቱ አንድ ሆኖ በአንድነት አሻፈረኝ ብሎ መነሳት መሆኑን ያምናል:: ወያኔ ጉልበቱ የኛ መከፋፈልና ለከፍፍሉ መመቸት መሆኑን ያምናል:: እኛ ስንተባበርና ልዩነታችንን ለመጠቀም የሚያደረገውን ሙከራ ስናከሽፍና አንዱ ላይ የሚደርሰውን ጥቃት የሁላችንም ነው ብለን የተነሳን እለት ወያኔ የለም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔ ዘረኞች አማራዉን አሁንም መድረሻ እያሳጡት መሆኑ ታወቀ

የአማራን ህዝብ፤ ታሪክና ባህል ለማጥፋት ትምህርታቸዉንና ስራቸዉን ትተዉ በረሀ የገቡት ዘረኞቹ የህወሀት መሪዎች የኢትዮጵያን ስልጣን ከጨበጡ ከሃያ አንድ አመታት በኋላ ዛሬም አማራዉን በየሄደበት እየተከታተሉ መድረሻ እየሳጡት መሆናቸዉን አዲስ አበባና በየክልሉ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባለፈዉ አመት አጋማሽ በደቡብ ክልል በጉራ ፈርዳ ወረዳ የጀመረዉን አማራዉን ነጥሎ የማጥቃት ዘመቻ ዘንድሮ በቤንምሻንጉል ጉሙዝ በመተከል ዞን በአዲስ መልክ የቀጠለ መሆኑን የገለጹልን ዘጋቢዎቻችን በወያኔ ልዩ ትዕዛዝ መተከልና አካባቢዉን ለቅቀዉ እንዲወጡ የታዘዙ የአማራ ተወላጅ የሆኑ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ክልሉን እየለቀቁ በመዉጣት ላይ መሆናቸዉ ታውቋል።

ሁኔታዉን በቅርብ ሆነዉ የሚከታተሉ የአይን እማኞች ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ቃል መሠረት ቁጥራቸዉ ከአምስት ሺ በላይ የሚሆን የአማራ ተወላጆች ልጆቻቸዉን፤ ከብቶቻቸዉንና የቤት ዉስጥ እቃቸዉን ይዘዉ አግራቸዉ ወደ መራቸዉ አቅጣጫ በመጓዝ ላይ ናቸዉ። በያዝነዉ ሳምንት መግቢያ ላይ ቁጥራቸዉ ከ500 በላይ የሆነ ተፈናቃይ አርሶ አደሮች የአማራ ክልል ዋና ከተማ ወደ ሆነችዉ ባህር ዳር የደረሱ ቢሆንም መገፋታቸዉንና እንግልታቸዉን አይቶ አቀባበል የሚያደርግላቸዉ በመጥፋቱ ለከፍተኛ ችግርና መከራ መጋለጣቸዉን ባህርዳር የደረሱት ተፈናቃዮች ለኢሳት ሬድዮና ቴሌቪዥን በሰጡት ቃል ተናግረዋል። የአማራ ህዝብ ተወካይ ነኝ ባዩ ብአዴን እወክላለሁ የሚለዉ ህዝብ ከየሚኖርበት ቦታ እየተገደደ ዉጣ ሲባልና በየሜካዉ ሲጉላላ አጁን አጣጥፎ ከመመልከት ዉጭ ሌላ ምንም ነገር ማድረግ አለመቻሉ ብአዴን የወያኔ አሻንጉሊት እንጂ በራሱ የቆመ ድርጅት አለመሆኑን ያሳያል ሲሉ አንድ ስማቸዉ እንዳይገለጽ የጠየቁን የህግ ባለሙያ ተናግሩ። የህግ ባለሙያዉ ይህንን የተናገሩት ከመተከል ተፈናቅለዉ ባህር ዳር የገቡትን የቅርብ ዘመዳቸዉን ይዘዉ አዲስ አበባ ሲገቡ ከግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ነዉ።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የሙስሊም ኢትዮጵያዊያን የተቃውሞ ድምጽ እንደቀጠለ ነው፣ በዲላ ከተማ እና በወልቂጤ የሚኖሩ ሙስሊሞች ተቃውሞ አሰሙ

ድምጻችን ይሰማ የሚል መፈክር አንግበው ከአንድ አመት በላይ እልህ አስጨራሽ የመብት ማስከበር ትግል በማድረግ ላይ የሚገኙት ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በትናንትናው እለትም በተለይም ፣ በዲላ እና በወልቂጤ የተቃውሞ ድምጻቸውን ሲያሰሙ መዋላቸውን አዲስ አበባ የሚገኘው ዘጋቢያችን በላከው ሪፖርት ገለጸ።

ከዚሁ ዘገባ ጋር በተያያዘ ከትናንትና በስቲያ ሌሊት በደሴ ከተማ ከ30 ሺ በላይ በራሪ ወረቀቶች መበተናቸውን ማህበራዊ የመገናና ብዙሀን ዜናውን ያሰራጩት መሆኑ ታውቋል። በፌስ ቡክ የተሰራጩት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የወያኔ ዘረና አገዛዝ የደሴ ሙስሊሞችን ለማዳከም የተለያዩ ሴራዎችን ሲሰራ መቆየቱን የተቃውሞው አስተባባሪዎች፣ መግለጻቸውንና መስጂዶቻችንን በመቀማት እና ኢማሞቻችንን በማባረር ከመስጂድ እንድንርቅ አድርጎን ቆይቷል፤ በዚህም ሳቢያ በደሴ የነበረው እንቅስቃሴ በተወሰነ መልኩ ተቀዛቀዞ የነበረ ሲሆን ዝምታው ለሊት ተሰብሯል፡ ማለታቸው ታውቋል።

ዘጋቢያችን እንደገለጸው በወረቀቶቹ ከሰፈሩት መፈክሮች ውስጥ "ኢትዮጵያን እየበጠበጠ ያለው የእስልምና አክራሪነት ሳይሆን የፖለቲካ አክራሪነት ነው፤"ኢቲቪ የውሸት ኢንዱስትሪ ነው!በእምነታችን አንደራደርም! አሚሮቻችንን ማሰር እኛን ማሰር ነው!፤ የእምነት መቻቻል እያደፈረሰ ያለው ሙስሊሙ ህብረተሰብ ሳይሆን መንግስት ነው" የሚሉት ይገኙበታል ብሏል፡፡

ሌሊት የተበተኑትን በራሪ ወረቀቶች ተከትሎ ዜጎችን ማሰርና ማንገላታት እንደመፍትሄ እየቀጠረ ያለው ጨካኝ የወያኔ አገዛዝ ፖሊሶች በተለያዩ ሰፈሮች ተበታትነው ሙስሊሞችን በማሰር ላይ እንደሚገኙ አስተባባሪ ኮሚቴው መግለጹ ታውቋል።

## ጋምቤላ አሁንም በወያኔ ወራሪ ሠራዊት እየታመሰች መሆኗ ተሰማ

በ1996 ዓም ከ400 በላይ አኝዋኮችን በግፍ የጨፈጨፈዉ የወያኔ ወራሪ ሠራዊትና ልዩ ኃይል ከሰሞኑ በብዛት ወደ ጋምቤላ በመዝመት ሠላማዊ ዜጎችን በተለይ የአካባቢዉን አርሶ አደሮች እየያዘ ማሰርና መግደል መጀመሩን ከአካባቢዉን እየሸሹ ጫካ የገቡ ዜጎች ለኢሳት ሬድዮና ቴሌቪዥን ስልክ እየደወሉ በሚልኩት ዜና ገለጹ። በተለይ ካለፈዉ እርብ ጀምሮ ፌዴራል ፖሊስ፤ መከላከያ ሠራዊትና የደህንነት ልዩ ሀይሎች ተቀናጅተዉ በጋራ በወሰዱት የማጥቃት እርምጃ ከቤት ቤት እየተዘዋወሩ ተቃዋሚዎችን ይረዳሉ ወይም ታጣቂዎችን ሊቀላቀሉ ይችላሉ ብለዉ የጠረጠሯቸዉን ሠላማዊ ዜጎች ማሰራቸዉንና እራሳቸዉን ለማዳን የሞከሩ ሰዎችን ተኩሰዉ መግደላቸዉን ከአካባባዉ የደረሰን ዜና ጨምሮ ያስረዳል። በአሁኑ ወቅት የወያኔ ወራሪ ሠራዊት በብዛት ወደ ጋምቤላና አካባቢዉ እየዘመተ ሲሆን የአካባቢዉ ህዝብም እራሱን ለማዳን ጫካ እየገባ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

የወያኔ ወራሪ ሠራዊት ካለፈዉ ዐርብ ጀምሮ በወሰደዉ የማጥቃት እርምጃ ከአስራ ሁለት በላይ ሠላማዊ ዜጎችን የገደለ ሲሆን ከሟቾቹ ዉስጥ አንድ የአካባቢዉ ተወላጅ የሆነ የአሜሪካ ዜጋ ይገኝበታል። የግንቦት ሰባት ድምጽ ዝግጅት ክፍል የወያኔ ጦር በአካባቢዉ ያደረገዉ ጭፍጨፋ እንደተሰማ በክልሉ የሚገኙ አንዳንድ ባለስልጣናትን ሰልክ ደዉሎ ሁኔታዉን ለማጣራት ሞክሮ ነበር ፤ ሆኖም የዝግጅት ክፍላችን ያናገረዉ ከፍተኛ የክልሉ ባለስልጣን በአካባቢዉ ምንም አይነት ግጭት የለም በማለት በአለም ዙሪያ የተሰራጨዉን እዉነት ለመካድ ሞክሯል። በሌላ በኩል አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ከፍተኛ የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣኖች የጸጥታ ሀይሎች ጋምቤላ አካባቢ የአማጽያንን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በሚል በወሰዱት እርምጃ አንድ የአሜሪካ ዜግነት ያለዉ ሰዉ መገደሉን ለአሜሪካ ኤምባሲ ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔው ኢህአዴግ እየተተራመሰ ነው፣ ድርጂት ተብየው እንደ ድርጅት አንድ ሆኖ መውጣት እንደተሳነው ተዘገበ

በተለይም የዘረኛው አገዛዝ አምባገነን መለስ ዜናዊ ከሞተ ወዲህ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የተከሰተው የውስጥ ሽኩቻ ከእለት እለት እየጨመረ መሄዱ በተከታታይ ሲዘገብ የቆየ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይሄው ትርምስ ከሰሞኑ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ በመድረሱ የወያኔው ኢህአዴግ እንደ ድርጅት አንድ ሆኖ መውጣት እየተሳነው እንደሆነ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደዘገበው በህወሀት ውስጥ ሁለት ቡድኖች ድርጅቱን ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ መጀመራቸው ከተዘገbe ከወራት በሁዋላ ችግሩ ከመቃለል ይልቅ እየጨመረ መምጣቱን አንድ የቀድሞ የህወሀት ነባር ታጋይ ለኢሳት ዘጋቢ ገልጸዋል ብሏል።

እንደ ኢሳት ዘገባ ነባር ታጋዩ፤ በስብሀት ነጋ በኩል ባሉ ሰዎች ወደ ድርጅቱ እንዲመለስ ጥሪ ቀርቦለት እንደነበር መጥቀሱንና ፤ እርሱ ግን አሻፈረኝ ማለቱን፣ እንዲሁም በድርጅቱ ውስጥ የሚታየው ክፍተት ለአደባባይ ባይበቃም፣ ህዝቡ የሚያየውና እየተነጋገረበት ያለ ጉዳይ መሆኑን ገልጹዋል ብሏል።

በተያያዘ መልኩም በአህዴድ በኩል ከመለስ ዜናዊ ሞት በሁዋላ የታየው ክፍተት እየሰፋ እንጅ እየጠበበ ሲሄድ አለመታየቱ ተገልጿል። በተለይም በከፍተኛ ህመም የሚሰቃየው ፕሬዚዳንቱን አለማየሁ አቶምሳን ለመተካት ቢፈለግም፣ በእርሱና በአፈ ጉባኤ አባዱላ ገመዳ ደጋፊዎች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ሌላ ፕሬዚዳንት ለመሾም ሳይቻል በመቅረቱ አለማየሁ በስልጣን ላይ እንዲቆይ መደረጉ ተገልጿል።

የወያኔው አገዛዝ አቀንቃኝ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ በትናንትናው እለት እትሙ ባወጣው ዘገባ ደግሞ አህዴድ የካቲት 20 ቀን 2005 ዓ.ም. ጠቅላላ ጉባዔውን ለማድረግ የተሰበሰበ ቢሆንም ፤ያልተጠበቁ አጀንዳዎች በመቅረባቸው ፤ ለኢሕአዴግ በሚቀርበው የሁለት ዓመታት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ብቻ በመወያየት ጉባዔውን ለሚቀጥለው ሳምንት አስተላልፎአል ብሏል። ጋዜጣው አክሎም የአህዴድ አባላት፣ ድርጅታቸው የተለያዩ ችግሮች ስላሉበት ጉዳዩ በአጀንዳ ተይዞ ውይይት እንዲደረግበት ጥያቄ ማቅረባቸውን ተከትሎ፣ የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ሰብሳቢዎች በድጋሚ ሌላ ስብሰባ እንደሚደረግና በዚያ ስብሰባ ላይ "አሉ" የተባሉ ችግሮችን በማንሳት መወያየትና መፍታት እንደሚቻል ቢናገሩም፣ ስምምነት ላይ አልተደረሰም ብሎአል።

## ጥቃት በየተራ እስከመቼ?

ባለፉት 21 የወያኔ የግዛት አመታት አይነቱና መጠኑ ይለያይ እንደሆነ እንጅ ጥቃት፣ ግፍ፣ በደልና እብሪታዊ የመብት ገፈፋ ያልደረሰበት ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ክፍል የለም። ገበሬው፣ የመንግስት ሰራተኛው፣ የፋብሪካ ሰራተኛና በየዘርፉ የእለት ጉርሱን አሳዶ የሚኖረው ሁሉ የወያኔን የሰቆቃ ግፍ በትር በየተራ አይቶታል፤ እያየውም ይገኛል። የኢትዮጵያ ህዝብ በድህነት አንጀቱ ለፍቶ ያቋቋማቸው ተቋሞቹ እየፈራረሱ ለወያኔ አገዛዝ እንዲመቹ ሆነው ሲጨፈላለቁም አይተናል።

ወያኔ ይህን ሁሉ ያደረገው "አንዱን በአንዴ" በሚል ስልት ነው። መምህራንን ሲያጠቃ የፋብሪካውን ሰራተኛ ተመልካች ያደርገዋል፤ ገበሬውን ሲያጠቃ ከተሜውን ዝም ይለዋል፤ ከተሜው ላይ ሲዘምት ገበሬው ተመልካች ይሆናል፤ ቤተክርሰቲያን ላይ ሲዘምት ቤተ ሙስሊሙ ይመለከተዋል፤ የቤተ ሙስሊሙ የበደል ተራ ጊዜ ቤተክርስቲያን ተመልካች ትሆናለች። ይህ ወያኔን እስከዛሬ ያደረሰው ስልት ነው።

አራዊታዊው የወያኔ አገዛዝ በተመቸውና ይጠቅመኛል ብሎ በአሰበ ሰአት ሁሉ የውብ ህዝብነት ምልክታችን የሆነውን የባህልና የቋንቋ ስብጥርነታችንን እርስ በርስ ለማናከሻነት ሊጠቀምበትም ሞክሯል፤ በተወሰነ ደረጃ አልሰራላቸውም ማለት ያስቸግራል።

ወያኔዎች ከፋፍሎ መግዛትንና በየተራ ማጥቃትን በኪነ ጥበብ ደረጃ አሳድገነዋል ብለው ያምናሉ። በህዝብ ወገን ያለነውም የዲሞክራሲና የነጻነት ሃይሎች ለዚህ አልተመቸንም ማለት ያስቸግራል። ይህንን ከፋፍሎ የማጥቃት ግፍ በጋራ ለመመከት ያደረግነው ጥረት ህዝባችን ላይ እየደረሰ ካለው ጥቃት ጋር ቢያንስ የሚመጣጠን አይደለም።

የወያኔ መሪዎች ዛሬ ስልታቸውን በማሻሻል አደገኛ ጭዋታ በቤተ እምነቶቻችን ዙሪያ መጫዎት ጀምረዋል። የቤተክርስቲያን እና የአቢያተ መስጊዶችን አስተዳደር በካድሬዎቻቸው ለመቆጣጠር ከሚያደርጉት ሳይጣናዊ ተግባር በተጨማሪ ህዝቡ ሃይማኖት ለይቶ እንዲባላ ለማድረግ በእጅጉ የሚቀፍ ፕሮፖጋንዳ እያካሄዱ ነው። ፍጹም ምሳሌያዊ የሆነውን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሲቪል መብት ጥያቄ እንደባዕድ መሳሪያነትና እንደ ሽብርተኝነት ለማሳየት እየሞከረ ይገኛል። በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሙሉ እጁን በማስገባት የተጀመረውን እርቀ ሰላም በማፍረስ የራሱን እንደራሴ ሰይሟል። ይህም አልበቃ ብሎት ለዘመናት በመከባበር የኖረውን ሙስሊሙንና ክርስቲያኑን እርስ በርስ ለማጋጨት ሴት ተቀን እየሰራ ይገኛል።

ዛሬ ከመቸውም በበለጠ ሀገራችን ወደማትወጣው አደጋ እየተገፋች ነው። ይህንን ወያኔ ያዘጋጀልንን የከፍፍልና ግጭት ድግስ ለመመከት ይበልጥ በአንድነት የምንቆምበት እና የምንታገልበት ግዜ ዛሬ ነው።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለወያኔ የ"ከፋፍለህ በየተራ ቀጥቀጥ" ፖሊሲ መድሃኒቱ አንድ ሆኖ በአንድነት አሻፈረኝ ብሎ መነሳት መሆኑን ያምናል። ወያኔ ጉልበቱ የኛ መከፋፈልና ለክፍፍሉ መመቸት መሆኑን ያምናል። እኛ ስንተባበርና ልዩነታችንን ለመጠቀም የሚያደረገውን ሙከራ ስናከሽፍና አንዱ ላይ የሚደርሰውን ጥቃት የሁላችንም ነው ብለን የተነሳን እለት ወያኔ የለም።

ግንቦት 7 ንቅናቄ ወያኔ በፈቃዱ የማይታረም ፋሺስታዊ አምባገነን መሆኑን ከተረዳ ሰንብቷል። በመሆኑም ወያኔን በማስገደድ ወይም በማስወገድ ነጻነታችንን መቀዳጀትና ነጻ ሀገር እንዲኖረን ማድረግ አለብን ብለን እናምናለን። ለዚህ ትግልም ማንኛውንም መሰዋእትነት ለመክፈል ተነስተናል። ነጻነትና ኮርተህ በነጻነት የምትኖርባት ሀገር እንድትኖርህ የምትወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ተቀላቀለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

### የወያኔ ዘረኞች አማራዉን አሁንም መድረሻ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የአዲስቱ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ መሪ የሆኑት አቶ አባንግ ሜቶ ከኢሳት ሬድዮ ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ በጋምቤላና በአካባቢዉ ያለዉን ወታደራዊ ዉጥረት ድርጅታቸዉ በቅርብ እንደሚከታተለዉ ተናግረዉ ከሰሞኑ በወያኔ ወታደሮች ተገደለ ስለተባለዉ የአሜሪካ ዜጋ አስፈለገዉን የክትትል መረጃዎች ለአሜሪካ የዉጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት መስጠጣቸዉን ተናግዋል። ዜጎችዋ በዉጭ አገር በሚደረጉ ወታደራዊ ግጭቶችና አመጾች ሲገደሉ ወይም ደብዛቸዉ ሲጠፉ ክፍተኛ ክትትል የምታደርገዉ ዩ ኤስ አሜሪካ አሁንም ጋምቤላ ዉስጥ በወያኔ ወታደሮች ተገደለ የተባለዉን ዜጋዋን ጉዳይ መከታተል መጀመሯን ለማወቅ ተችሏል። በቅርቡ የኦባማ አስተዳደር ከአሸባሪዎች ጎን ተሰልፈዉ በሚዋጉ የአሜሪካ ዜጎች ላይ የሚወስደዉን አርምጃ በተመለከት ሾልኮ የወጣዉ መረጃ ኮንግሬሱን ጨምሮ አያሌ አሜሪካኖችን እንዳስቆጣ የሚታወቅ ሲሆን፤ ይህ ከሰሞኑ ጋምቤላ ዉስጥ የተገደለዉ አሜሪካዊ ጉዳይ ይበልጥ በተሰማና በታወቀ ቁጥር ወያኔ ላይ መዘዝ ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ።

### ጋምቤላ አሁንም በወያኔ ወራሪ ሠራዊት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የአዲስቱ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ መሪ የሆኑት አቶ አባንግ ሜቶ ከኢሳት ሬድዮ ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ በጋምቤላና በአካባቢዉ ያለዉን ወታደራዊ ዉጥረት ድርጅታቸዉ በቅርብ እንደሚከታተለዉ ተናግረዉ ከሰሞኑ በወያኔ ወታደሮች ተገደለ ስለተባለዉ የአሜሪካ ዜጋ አስፈለገዉን የክትትል መረጃዎች ለአሜሪካ የዉጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት መስጠጣቸዉን ተናግዋል። ዜጎችዋ በዉጭ አገር በሚደረጉ ወታደራዊ ግጭቶችና አመጾች ሲገደሉ ወይም ደብዛቸዉ ሲጠፉ ክፍተኛ ክትትል የምታደርገዉ ዩ ኤስ አሜሪካ አሁንም ጋምቤላ ዉስጥ በወያኔ ወታደሮች ተገደለ የተባለዉን ዜጋዋን ጉዳይ መከታተል መጀመሯን ለማወቅ ተችሏል። በቅርቡ የኦባማ አስተዳደር ከአሸባሪዎች ጎን ተሰልፈዉ በሚዋጉ የአሜሪካ ዜጎች ላይ የሚወስደዉን አርምጃ በተመለከት ሾልኮ የወጣዉ መረጃ ኮንግሬሱን ጨምሮ አያሌ አሜሪካኖችን እንዳስቆጣ የሚታወቅ ሲሆን፤ ይህ ከሰሞኑ ጋምቤላ ዉስጥ የተገደለዉ አሜሪካዊ ጉዳይ ይበልጥ በተሰማና በታወቀ ቁጥር ወያኔ ላይ መዘዝ ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ።

## የወያኔው ኢህአዴግ እየተተራመሰ ነው፣ ድርጂት ተብየው እንደ ድርጅት አንድ ሆኖ መውጣት እንደተሳነው ተዘገበ

በተለይም የዘረኛው አገዛዝ አምባገነን መለስ ዜናዊ ከሞተ ወዲህ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የተከሰተው  የውስጥ ሽኩቻ ከእለት እለት እየጨመረ መሄዱ በተከታታይ ሲዘገብ የቆየ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይሄው ትርምስ ከሰሞኑ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ በመድረሱ የወያኔው ኢህአዴግ እንደ ድርጅት አንድ ሆኖ መውጣት እየተሳነው እንደሆነ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደዘገበው በህወሀት ውስጥ ሁለት ቡድኖች ድርጅቱን ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ መጀመራቸው ከተዘገbe ከወራት በሁዋላ ችግሩ ከመቃለል ይልቅ እየጨመረ መምጣቱን አንድ የቀድሞ የህወሀት ነባር ታጋይ ለኢሳት ዘጋቢ ገልጸዋል ብሏል። እንደ ኢሳት ዘገባ ነባር ታጋዩ፤ በስብሀት ነጋ በኩል ባሉ ሰዎች ወደ ድርጅቱ እንዲመለስ ጥሪ ቀርቦለት እንደነበር መጥቀሱንና ፤ እርሱ ግን አሻፈረኝ ማለቱን፣ እንዲሁም በድርጅቱ ውስጥ የሚታየው ክፍተት ለአደባባይ ባይበቃም፣ ህዝቡ የሚያየውና  እየተነጋገረበት ያለ ጉዳይ መሆኑን ገልጹዋል ብሏል።
በተያያዘ መልኩም በኦህዴድ በኩል ከመለስ ዜናዊ ሞት በሁዋላ የታየው ክፍተት እየሰፋ እንጅ እየጠበበ ሲሄድ አለመታየቱ ተገልጿል። በተለይም በከፍተኛ ህመም የሚሰቃየው ፕሬዚዳንቱን አለማየሁ አቶምሳን ለመተካት ቢፈለግም፣ በእርሱና በአፈ ጉባኤ አባዱላ ገመዳ ደጋፊዎች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ሌላ ፕሬዚዳንት ለመሾም ሳይቻል በመቅረቱ አለማየሁ  በስልጣን  ላይ እንዲቆይ መደረጉ ተገልጿል።

የወያኔው አገዛዝ አቀንቃኝ የሆነው ሪፖርተር  ጋዜጣ በትናንትናው እለት እትሙ ባወጣው ዘገባ ደግሞ ኦህዴድ የካቲት 20 ቀን 2005 ዓ.ም. ጠቅላላ ጉባዔውን ለማድረግ የተሰበሰበ ቢሆንም ፤ያልተጠበቁ አጀንዳዎች በመቅረባቸው ፤ ለኢሕአዴግ በሚቀርበው የሁለት ዓመታት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ብቻ በመወያየት ጉባዔውን ለሚቀጥለው ሳምንት አስተላልፎአል ብሏል። ጋዜጣው አክሎም የኦህዴድ አባላት፤ ድርጅታቸው የተለያዩ ችግሮች ስላሉበት ጉዳዩ  በአጀንዳ ተይዞ ውይይት እንዲደረግበት ጥያቄ ማቅረባቸውን ተከትሎ፣ የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ሰብሳቢዎች በድጋሚ ሌላ ስብሰባ እንደሚደረግና በዚያ ስብሰባ ላይ "አሉ" የተባሉ ችግሮችን በማንሳት መወያየትና መፍታት እንደሚቻል ቢናገሩም፣ ስምምነት ላይ አልተደረሰም ብሎአል።

## ልማት/ዕድገት - ልማት መነሻ ነጥብ እንጂ ማደግን ማሳያ አይደለም!

(በብስራት ገብሬ)

ልማት እና እድገት ተያያዥነት ይኑራቸዋል እንጂ ፍፁም ይለያያሉ፤ ልማት ለዕድገት የሚወስደን መሰላል እንደ ማለት ነው፡፡ ሁሉን ነገር አቅሎ ምቹና የተስተካከለ ሲደረግ. . . ነገሮች አልጋ በአልጋ ሆነው ‹ ዕድገት› ወደሚባለው ቀጣይ ክፍል ይወስዱናል፡፡ ይህን ለማድረግ ሁሉም ሰው ህብረት ሊኖረው ይገባል፡፡ ልማት ላይ መግባባት እና ተነሳሽነት ከሁሉም ይጠበቃል፡፡ እነዚህን ማሟላት ስንችል የሚፈለገውን ግብ መምታት ይቻላል፡፡ ለዛም ነው ከላይ ልማት መነሻ ነጥብ እንጂ ማደግን ማሳያ አይደለም ብዬ የተነሳሁት፡፡ የመለወጥ ተስፋዎች፤ የማደግ ጭላንጭሎች ሲታዩ ልማቱ ውጤታማ እንደሆነ ማሰብ ይቻላል፡፡ ግልፅ ለማድረግ ያህል አንድ ሀገር ብዙ የሰው ሀይል ቢኖራት ፤ የበዛ የማዕድን ክምችት ቢኖራት፣ ለም እና ምቹ መሬት ዙሪያውን ቢከባት ይህንን አስተባብሮ በዘመንኛው አነጋገር ዘላቂነት ባለው መንገድ የህዝቡን የአስተሳሰብ ፣ የአኗኗር ዘይቤ የተሻለ በማድረግ ፣ እንዲሁም የደህንነት ጥራቱንም ከፍ በማድረግ ወደ አንድ ጥንካሬ ተሸጋግሮ እስካልተገኘ ድረስ ዕድገት አለ ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፡፡ አለ የምንለው ከላይ የተዘረዘሩት በጥቂቱም ቢሆን ሲሟሉ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህንን ለማምጣት የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ናቸው ልማታዊ እንቅስቃሴዎች የምንላቸው፡፡ እንግዲህ በዚህ ሂደት ውስጥ ሰው የሚያየው፣ የሚቀምሰው፣ የሚያሸተው፣ የሚያነበው፣ የሚወደው፣ የሚጨነቅለት ነገር ሊኖር ይገባል፡፡ እነዚህ ነገሮች ከተጓደሉ ለስራ የሚኖረው ተነሳሽነት ይቀንሳል፤ ለሀገር ያለው ፍቅር ይዳከማል፤ በህብረት በአንድነት ማሰብ ትቶ ግለተኝነትን ወደ መፈለግ ይኬዳል፡፡ ይህ ሁሉ ደግሞ ወደ አንድ ስንደምረው ያልተደራጀ እና ህብረት የሌለው ስለሚሆን በአንድም ይሁን በሌላ ግዜ ለመፍረስ፣ ለመውደቅ የተመቻቸ ነው፡፡ ዘላቂነት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡ እድገትንም እንደተፈለገው ሳይሆን ተናፋቂ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ልማት ግብዓት እንጂ ውጤት ስላልሆነ፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ለማስወገድ ደግሞ ደህንነት፣ የሰብአዊ መብቶች ማለትም የመናገር፣ የመፃፍ፣ ከቦታ ቦታ በነፃነት እየተዘዋወሩ መኖርን ( በሰላም ወጥቶ መግባት) እና ሌሎችም ከምንም በላይ ለአንድ ሀገር ልማት እና ዕድገት መፋጠን እና ዘላቂት መኖር ዋልታዎች በመሆናቸው አትኩሮት ሊሰጣቸው ግድ ይላል፡፡ እነዚህ በጥቂቱ ሲሟሉ መኖርንም ሙሉ ማድረግ ይጀምራሉ፡፡ ለራስ ከሚባለው አስተሳሰብ አስወጥቶ ለቤተሰብ፣ ለአካባቢ፣ ለህዝብና ለሀገር እንድናስብ እንድንቆረቆር እንድንሞት ያደርጋል፡፡ እዚህ ላይም የመምረጥ ነፃነትም ሳይዘነጋ ማለት ነው፡፡ እስቲ ከዚህ ጉዳይ እንውጣና:: ዐፄ ምኒልክ የተናገሩትን ላስታውስ

‹‹ . . . . እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፋፍቶ አኖረኝ፡፡ እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ፡፡ እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ስለእኔ ሞት አላዝንም፡፡ ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ከእንግዲህም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም፡፡

አሁንም ሀገር የሚያጠፋ ሃያማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚሐብሔር የወሰነልንን የባሕር በር አልፎ መጥቷልና እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ የሰውንም መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር፡፡ አሁን ግን በእግዚሐብሔር ረዳትነት ሀገሬን አሳልፌ አልሰጠውም፡፡ ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልኩህ አይመስለኝም ፡፡ አንተም እስካሁን አላስቀየምኸኝም፡፡ ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ፡፡ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ ለሚስትህ ለሀይማኖትህ ስትል በሀዘን እርዳኝ፡፡ ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ፡፡ አልተውህም፡፡ ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም፡፡ ዘመቻዬ በጥቅምት ነውና የሸዋ ሠው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ፡፡ ››

ይህ የዐፄ ምኒልክ ንግግር እጅግ ከሚማርኩኝና ሁሌም ባነባቸው ከማልሰለቻቸው ከመሪዎቻችን ንግግሮች ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ በጣም ብዙ ትርጎሞችም አሉት፡፡ በዚህ ዘመን ይህን መሳይ ንግግር ባይጠበቅም አሁን ለምናወራለት ሀሳብ ግን ብዙ ትምህርቶችን የሚሰጥ ነው ብዬ ስላሰብኩ አቀረብኩት፡፡ የዐፄው ንግግር መነሻ የጣልያን ጦር አገራችንን መውረሩ ነው፡፡ መጨረሻው ደግሞ የተገመተው ሳይሆን በተቃራኒው በኢትዮጵያ አሸናፊነት መጠናቀቁ ነው፡፡ ይህን ነው እኔ ዕድገት ብዬ የምጠራው፡፡ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ፣ አንድ ዓይነት ፍላጎት፣ አንድ ዓይነት ተነሳሽነት የተንፀባረቀበት ሆኖ ምንም አይነት ነገር ቢመጣ በዚህ መልክ ከተሄደ የሚፈለገውን ግብ መምታት እንደሚቻል አስተምሮ የራሱን አሻራ ትቶ ያለፈ ድንቅ ታሪክ ነው፡፡ለአሁኑ ማንነታችን መስታዎት ነው፡ እምነት የሁሉ መተሳሰሪያ ገመድ ነው፤ የጥንካሬ መነሻም መድረሻም በመሆን ያገለግላል፡፡ እምነት ያለው ሰው ሁሌም ጠንካራ ነው፡፡ ለመኖር እምነት ያስፈልገናል ለመተንፈስ እምነት ያስፈልጋል፡ ፡ለመብላት እምነት ያስፈልጋል፡፡ ወዳጅ ለማፍራት እምነት ያስፈልጋል፡፡ ለሁሉም እምነት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ነው ዐፄ ምኒልክ‹‹ . . .ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ፡፡ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ ለሚስትህ ለሀይማኖትህ ስትል በሀዘን እርዳኝ፡፡. . . ›› ያሉት ፡፡ ሀይማኖት የእምነት ማቀፊያ ነው ፡፡ ማቀፊው ሲመታ አስኳሉ እንደሚፈሰው እንቁላል ማንም ሀይማኖቱ እንዲነካ አይፈልግም፡፡ ሀይማኖቱ ተነካ ማለት እምነቱ ተነካ ማለት ነው፡፡ እምነቱ ሲነካ ደግሞ ማንነቱ አስተሳሰቡ ተነካ እንደማለት ነው፡፡ ይህም የሚያስከትለው ጣጣ እና ተያይዞ የሚመጣው ነገር ብዙ ነው፡፡ ቅዱስ መፅሐፍም ሁሉም ስለሀይማኖቱ እንዲቆም ይመክራል፡፡ (1ኛ ቆሮ.16፤13/የሐዋርያት ስራ 14፤22/ ዕብ.4፤14 ሌሎችም የበዙ) በአድዋው ድል ችግረኞች፣ ደሀዎች ኋላ ቀር መሳሪያዎችን ተጠቃሚ የሆኑ ህዝቦች አውሮፓውያኑን ሲረቱ. . . ሲማርኩ. . . ሲገርፉ. . . ሲያባርሩ ማየት የተለመደ አይደልም፤ የለምም፡፡ እዚህ ግን ሆኗል፡፡ ቅኝ ላለመገዛት ሀገርን ሐይማኖትን ላለማጣት በህብረት መስዋዕት መሆንን አስተምሯል፡፡

በቅርብ ጊዜያት በግብፅ፣ በቱኒዚያ የተነሱትን መሪዎቻቸውን ለማስነሳት ያደረጉትን ተጋድሎ ስናይ ምን አጥተው ነው? ምን ጎሎባቸው ይሆን ብለናል፡፡ ይህም በመነሻዬ የተነሳሁትን ሀሳብ ይደግፋል፡፡ በህግ መገዛት እንዳለ ሆኖ ምንም ያህል በሀብት ደረጃ ጣራ ላይ ብንወጣ ውስጣዊ መሻት( ሰብዓዊ መብቶች ) የሚባሉትን ተያይዘው የሚመጡትን ጥያቄዎች ግን መመለስ ግድ ነው፡፡ ሰው በባህሪው ነፃነትን ይሻል፡፡ የሚፈልገውን ማድረግ ፣ ያሻውን መሆን ፣ የሚፈልገውን መውደድ ፣ የሚፈልገውን መጥላት፣ የሚፈልገውን ማምለክ፣ የሚፈልገውን መስራት፣ የሚፈልገውን አስተያየት መስጠት. . .ሌላም ሌላም፡፡ እዚህም ላይ ነው እንግዲህ ማንም መነካት የማይፈልገው፡፡ ድንበሬ ያለውን ቦታ ሲነኩበት፣ ልክ አይደለህምና እንደዚህ ሁን. . . . አትሁን. . . ሲባል፣ የራሴ ነው የሚለው ሲወሰድበት ሲጣልበት. . . ያኔ ፀብ ይጀመራል፡፡

‹‹ . . . ዓለም በሀይማኖት ጉዳይ ተዋጊ አይደለም፤ እንዲያውም አዋጊ ነው፤ ዓለም በፈለገው አቅጣጫ ነው የሚሰራ. . . የመንፈሳዊ ሕይወት ፍቅር የለውም፡፡ ሁሉም በዲሞክራሲ መብት ይለይለት ባይ ነው፡፡ . . .›› ይላሉ አባ ገ/መድህን ከበደ በ‹‹ ከህግ ስራ የሆኑት ሁሉ ከርግማን በታች ናቸው፡፡ (ገላ.3፤10) በሚለው መፅሐፋቸው፡፡

ዓለም ለሀይማኖት እሴቶች ቦታ እያጣች በመምጣቷ ቤተክርስቲያናት ሲቃጠሉ፣ ሲዘረፉ፣ የሌባ ማፍሪያ ምንጭ ሲሆኑ እንደቀድሞው አያሳስባትም፡፡ ክብርም አትሰጥም፡፡ መንግስታትም ሆነ መሪዎች ለመንፈሳዊ አስተሳሰብ ሳይሆን ለዲሞክራሲ አስተሳሰብ (ለዓለማዊ አስተሳሰብ) ቅድሚያ መስጠት ጀምረዋል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው አሁን አሁን በሀገራችን እያየን ያለነው ጉዳይ ነው፡፡ ዕድገትን ማምጣት የሚቻለው ገዳሞችን በመረበሽ፣ በማፍረስ የሸንኩርት ወይም የስኳር ልማት በማስጀመር ይመስላቸው ጀምሯል ፡፡ እንዲሁም የቤተክርስቲያንን ቦታ እና ይዞታ በመውሰድ ለአንድ ባለሀብት መሸጥ የተለመደ እየሆነ ነው ከዚህም አልፎ ስለ ሀገር ዕድገት የሚታሰበው ቤተክርስቲያን ታሪኬ ናቸው ቅርሶቼ ናቸው የምትላቸው ሀብትና ንብረቶቿን በማፍረስ እየሆነ ነው ፡፡ ከላይ ስነሳ እንዳልኩት ልማት ማለት ትልቅ ለመሆን ለሚደረግ ሽር ጉድ ነው፤ሂደት ነው፡፡ የስኳር ልማትም ይኑር፣ የአበባ ልማትም ይስፋፋ፣ የመንገድ፣ የውሃ፣ የኃይል ማመንጨዎች ና የመኖሪያ ቤቶች ይገንቡ፡፡ እነዚህ ነገሮች ሲሟሉ ነው ወደ ተፈለገው አቅጣጫ በፍጥነት መሄድ የሚቻለው፡፡ ዕድገትንም ማቅረብ የሚቻለው፡፡ ነገር ግን ይህ ወይም ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ብቻም አይደልም ለእድገት መሰረቱ፡፡ መንፈሳዊ አስተሳሰብም ለዕድገት ቁልፍ ነው፡፡ ልንጠብቀውና ሁሌም ከግምት ውስጥ ልናስገባው ይገባል፡፡

አድገዋል የምንላቸው አሜሪካኖች የእምነት እሴቶች እና ውበቶች አጥተን በገንዘብ ወረቀታቸው ላይ ‹‹ IN GOD WE TRUST/ በእግዚሐብሔር እናምናለን ›› ብለው ፅፈዋል፡፡ በተጨማሪም ‹‹ GOD BLESS AMERICA/ እግዚአብሔር አሜሪካን ይባርክ ›› ብለውም መሪዎቿ በእያንዳንዱ በየንግግራቸው ያስገባሉ፣ ይላሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው ምንም ብናድግ ምንም ብንበለፅግ የፈጣሪ እርዳታ አስፈላጊ መሆኑን እንዲሁም ያለ እምነት ሀገር እንደማትኖርና እግዚአብሔርን ሳያምኑ መኖር የትም እንደማያደርስ ነው፡፡ ግን አሜሪካኖች እንደዛ ናቸው ወይ ከተባለ አዎ ወይም አይደሉም ነው መልሱ፡፡ እኔ ላተኩር የፈለኩት ግን ‹‹ ማመን ›› የሚለው ቃል ትልቅ ቦታ እንዳለውና እምነት ወሳኝ መሆኑን ነው ፡፡ እነሱ ያላቸውን ተቀብለው እና አስማምተው ሲኖሩ እንደእኛ በእምነት የፀኑ እና የተገነቡ ሀገራት ደግሞ ያላቸውን በማፍረስ በአንድ ግዜ ማደግን ይሻሉ፡፡ ለዓመታት ስናኮራፋ ቆይተን ድንገት ሁሉ አማረሽ እየሆንን ነው፡፡ ችኩል የሆነ አስተሳሰብ ሲበዛ እየተንሰራፋ ነው፡፡ ማፍረስ፣ ማጥፋት፣ ማውደም ብቻ እየሆነ ነው፡፡ ልማት የሚል ቁንፅል መነሻ ለብዙ ጥያቄዎች መነሻ እየሆነ ነው፡፡

አንድም እምነት ልማትን አይቃወምም፡፡ ምን አልባት ሊባል የሚችለው ልማት ከመንፈሳዊ ህይወት ከመንፈሳዊ አስተሳሰብ ጋር ቢሆን መልካም ይሆን ነበር ነው፡፡ በተለይ ኢትዮጵያን እና ያለፈ ታሪኳን ብንመለከት ምን ያህል በእምነት የጠነከረች እና የስልጣኔ( እድገት) ጣራ የነካች እንደነበረች ነው የሚያሳየን፡፡ ድሮ በዘመነ መሳፍንትም ይሁን ዘመናዊቷን ኢትዮጵያ ማለትም ከ1847 ጀምሮ እስከ ንጉስ ሀይለ ስላሴ ግዜ ብናይ ሁሉም ማለት በሚያስችል ሁኔታ ለቤተክርስቲያን ክብርና በውስጧም ላሉ ቅርሶቿና ትውፊቶቿ የሚጠነቀቁ ነበሩ፡፡ የአክሱም ሀውልትን ያየ፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የጎበኘ፣

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ኢትዮጵያ ዉስጥ ህዝብንና አገርን የሚጠቅም ስራ መስራት እንደማይቻል የጀርመን ፋውንዴሽን ዳይሬክተር ተናገሩ

ባለፈዉ አመት መጨረሻ አካባቢ የወያኔ አገዛዝ አላሰራ ብሎት ኢትዮጵያን ለቅቆ የወጣዉ ሄንሪክ ቦል ፋዉንዴሺን የተበላዉ የጀርመን ምግባረ ሰናይ ድርጀት ዋና ዳይረክተር ኢትዮጵያ ዉስጥ ምንም አይነት የህዝብን ኑሮ የሚለዉጥ ስራ መስራት አይቻልም ሲሉ የወያኔን አገዛዝ ደንቃራነት አወገዙ። ሚስትር ፓትሪክ በርግ የተባሉ የምግባረ ሰናዩ ድርጅት ዋና ዳይረክተር ይህንን የተናገሩት ድርጅታቸው ከኢትዮጵያ የለቀቀበትን ምክንያት ብሉምበርግ ለተባለዉ የዜና ማሰራጫ ተቋም ባስረዱበት ወቅት ነዉ። እንደ ዳይረክተሩ አባባል ኢትዮጵያ ዉስጥ ሌላ ቀርቶ የጥበብ ስራ እንኳን በአሁኑ ጊዜ በጥርጣሬ የሚታይ ነው፣ እኛ የምንሰራዉ ስራ ደግሞ ከሰብዓዊ መብቶች መከበር ጋር በቀጥታ የተያያዘ ስለሆነ አገዛዙ በፍጹም አልወደደዉም ካሉ በሁዋላ ይህንን ከመብት ጋር የተያያዘውን ስራችን አቁሙ በመባላችን ኢትዮጵያን ለቅቀን ወጥተናል" ብለዋል።

የኢትዮጵያ መንግስት ከጾታ እኩልነትና ከሰብዓዊ መብት ጥበቃ ጋር የምንሰራዉን ስራ ለመግታት እራሱ ከጻፈዉ ህገመንግስት ጋር የሚጻረር ህግ አዉጥቷል ያሉት ሚስተር ፓትሪክ በርግ አገዛዙ ነገሮችን የሚያየዉ ህዝብን ይጠቃማል ወይስ ይጎዳል ብሎ ሳይሆን ከራሱ የስልጣን ዘመን ጋር እያስተያየ ስለሆነ ከዚህ አይነት አገዛዝ ጋር ምንም አይነት ህዝብንና አገርን የሚጠቅም ስራ መስራት አይቻልም ብለዋል።

ድርጀቱን ወክሎ ከሚስትር ፓትሪክ በርግ ጋር የተወያየዉ የብሉምበርጉ ሚስትር ዊልያም ዳቪሰን ደግሞ የሲቪክ ሶሳይቲና ቻርቲ ህግ የሚቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ውርስ መሆኑን ተናግሮ ህጉ የወጣዉ ከመንግስት የተለየ ሃሳብ ያላቸውን ተቃዋሚዎችና ምግባረ ሰናይ ድርጅቶችን ለመቆጣጠር ነዉ በማለት አምነስቲ ኢንተርናሽናልን በመጥቀስ ተናግሯል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሂውማን ራይትስ ዋች የአፍሪካ ክፍል ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ዳንኤል በቀለ ፣ መንግስት ያወጣው የሲቪክ ሶሳይቲና ቻሪቲ ህግ ዋና ግቡ በአገር ውስጥ ካለው ፖለቲካና ሲቪክ ሶሳይቲ ስራ ጋር የተያያዘ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ መንግስት ቃል አቀባይ የሆነዉ ጌታቸው ረዳ ደግሞ ህጉ በሙስና የተዘፈቁ የሲቪክ ድርጅቶችን ለመቆጣጠር ተብሎ የተረቀቀ መሆኑን በመግለጽ፣ የወያኔን አቋም አንጸባርቋል።

## ልማት/ዕድገት - ልማት መነሻ ነጥብ እንጂ ማደግን . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

የፋሲለደስን ህንፃ ቤተመንግስት ያየ. . . . በዓለም የንግድ ግንኙነት ላይ የነበረንን ተፅዕኖ እና ተሰሚነት የሚያውቅና የሰማ ሁሌም መገረሙ መደነቁ አይቀርም፡፡

የጥንት የሮም ጳጳሳትና የካቶሊክ አባቶችም ወታደሮችን ድል አድርገው እንዲመጡ ባርከውና መርቀው እግዚአብሔር ከእነሱ ጋር እንዲሆን ተመኝተው ወደ ጦር ግንባር እንደሚልኳቸው ታሪክ ይናገራል፡፡ እግዚአብሔርን ሳይዝ የሚሄድ ወታደር ደግሞ መረታቱ ስለማይቀር ኢትዮጵያውያም የውጪ ጠላቶች ሲመጡ ታቦታትን በመሸከም የጦር አውድማዎች ላይ ጠላትን ድባቅ መተው ድልን ይጎናፀፉ ነበር፡፡ ሁሌም አሸናፊዎች ነበሩ፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ትልቁ እና ሁሌም የምንኮራበት የአድዋ ድልም ከአባቶቻችን ታላቅ ጀግንነት ጀርባ የቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት እንደ ነበረ ግልፅ ነው፡፡ እምነት ያለው ያሸንፋል፡፡

ታዲያ ዛሬ ምን ነካን

የዚህ ሁሉ ታሪክ ባለቤትና ድንቅ የጀብደኝነት ታሪክ እና የጀግኖች መናኸሪያ እንደነበረች ሲታይ . . . ዛሬ ምን ነካቸው ኢትዮጵያውያንን ያስብላል፡፡ እግዚአብሔር ሁሌም ኢትዮጵያን ስለሚጠብቅ እንጂ አሁን በዚህ ግዜ ጠላት ቢመጣ ምን እንደሚውጠን ማሰብ ቀላል ነው ነበር፡፡ የአባቶች ያቆዩት ሞራል እና በሰው ብዛት ካላሸነፍን በስተቀር እምነቱንማ ችላ እያልንና እየጣልን ነጥተናል፡፡ አውሮፓዊ አስተሳሰብ፣ ስግብግብነት ፍቅር ማጣት በሀገሪቱ ስር እየሰደደ ነው፡፡ ያ ሁሉ ስልጣኔ እና ዕድገት በነበረ ሰዓት ኢትዮጵያ አይደለም የራሷን ልትጥል የሌላ ዕምነት ተከታዮችንም በእንግድነት የምትቀበል በራሷ የምትኮራ፣ ኢትዮጵያዊነት በራሱ ኩራት የሆነባት የበሰለች ሀገር ነበረች፡፡ አሁንም መሆን ይቻላል፡፡

‹‹ ለወገንና ለሀገር የሚጠቅም ስራ ስሩ፤ለሆዳችሁ አትደሩ፣
ፍቅርና መቻቻል አይለያችሁ፡፡›› አቡነ ጴጥሮስ

ዐፄ ምኒሊክ በማርያም ለምነው ያቆሟት ኢትዮጵያ፣ አቡነ ጴጥሮስን የመሠሉ ታላላቅ ሠማዕታት የተሰዉላት፣ እንደነ አበበ ቢቀላ በባዶ እግራቸው ደማቸውን የዘሩላት የሮጡላት ፣ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ቀን ከሌት ሰላም ውላ ሰላም እንድታድር በየዋሻው ገዳማቱ ሰውን ርቀው ሸሽተው በፀሎት ፈጣሪን የሚማፀኑላትን ውድ ልጆች የያዘች አሁን አሁን ግን እነዚህን ውድ ልጆቿን ለምን እንደማታከብር ግልፅ አይደለም፡፡ እነዚህ የተከበሩ ግለሰቦችና ሠማዕታት ቅድሚያ ለሀገራቸው ለሀይማኖታቸው ቦታ የሚሰጡ፣ ክብር ያላቸው ናቸው ፡፡ እኛ ያልሰራነውን ተአምር እና ጀብደኝነት የፈጸሙና እናት ሀገራችንን ላስከበሩ ሁሉ አክብሮትና ቦታ መስጠት ያስሞግስ ይሆን እንጂ አያስወቅስም፡፡ የታሪክ ተወቃሽ ከመሆን ያድነን፡፡ አነሰም በዛም የሀገርን ስምና ዝና ከፍ ያደረጉ በመሆቸው ክብር ይገባቸዋል፡፡ አዲስ አበባ በትልልቅ የመንገድ አደባባዮች የተሞላች ናት፡፡ በድርጅት ማስታወቂያዎች ከመሙላት ይልቅ በሀገር በህዝብ የተከበሩ ግለሰቦችን ለማስታወስ ሀውልት ሊሰራላቸው እንጂ ታሪካቸው እንዲጠፋ መሯሯጥ የለብንም፡፡ የእነርሱን ታሪክ በማጥፋት ምን ዓይነት ትውልድ ልንገነባ እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ ዕምነት የሌለው?? ሀገሩን የማይወድ እና ለማንም አሳልፎ የሚሰጥ?? ከንቱ ትውልድ ከማፍራት አንተርፍም፡፡ ይህ ደግሞ ለማንም አይጠቅምም፡፡ እስቲ ይታየን ይህ ትውልድ እውነት እባክህን ናና ሀገርህን አልማ፣ አሳድግ ቢባል ይሰማል?? የሀገርህን ባህልና ስርዓት ተማር ቢባል ፍቃደኛ ይሆናል?? ዐፄ ሚኒሊክ የተናገሩትን "… ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ፡፡ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ ለሚስትህ ለሀይማኖትህ ስትል በሀዘን እርዳኝ፡፡ ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ፡፡ አልተውህም።" ቢባል አይሰቅም?? እኔ ስጋት አለኝ፡፡

ለዚህ ሁሉ መፍትሄ የምትሰጠውና ዓለማዊውንም መንፈሳዊውንም የምታገናኝና ድልድይ ሆና ትልቅ ሚና በመጫወት በስነምግባር የታነፀ፣ ፈጣሪን የሚፈራና ሀገሩን የሚያከብር ህዝብን የሚወድ፣ መንፈሳዊ ፍቅር ያለበት፣ ለስራ ተነሳሽ የሆነ ትውልድ የምታፈራና የምታንፀው ደግሞ ቤተክርስቲያን ናት፡፡ እንዲሁም ገዳማት ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የሐይማኖት ተቋማት ናቸው፡፡ ስለዚህ ቅድሚያ አትኩሮታችን መጀመር ያለበት እነዚህን ተቋማት በማክበርና አብሮ ለመስራት በመዘጋጀት ነው፡፡

የብዙ ሀይማኖት መገኛ፣ የብሔር ብሔረሰቦች ጥርቅም ወዘተ. . . እንላታለን፡፡ ይሁን መልካም ነው፡፡ ነገር ግን እንደ ናይጄሪያውያን የበዛ የዕምነትና የሀይማኖት መሞከሪያ ቤተ-ምርምር (laboratory) መሆን ሀገር ከማሳደግ ይልቅ ረብሻ እና ጦርነትም ከማስፋፋት የዘለለ ፋይዳ የለውም፡፡ መግባባት መቻል በራሱ የአንድ ሀይማኖት መገለጫ መሆን አለበት፡፡ ሁሉም እየዘለለ በሚያነሳው ሀሳብ አንዱ መበደል የለበትም፡፡ ሁሉንም በእኩል ለማየት ሲባል የአንዱ እምነት ተቋም ሀብትና ንብረት ለሌላው መሰጠት የለበትም፡፡ በየትኛው ፈጠራችን ነው? የትኛው ለውጣችን ይሆን የእምነት ተቋሞች ላይ እጃችንን እንድናነሳ የሚያደርገን? የትኛው የዲሞክራሲ አስተሳሰብ ነው ለቅርሶች ቦታ እንዳንሰጥ የሚገፋን. . . መልስ የሚሻቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በእንደዚህ ሁኔታ ምንም ዓይነት ልማትም ሆነ ዕድገት ፈፅሞ መታሰብ የለበትም፡፡ መቀመጫን በመርፌ ወግቶ አረፍ በል እንደማለት ነው፡፡ እንደማሾፍም ነው የሚቆጠረው፡፡ ለማደግ ወይም ለልማት የምናመጣው ሀሳብ ያለንን የሚያጠናክር እንጂ የሚያዳክም መሆን የለበትም፡፡ ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን ሲባል የማይነካ እየተነካ. . . የማይባል እየተባለ. . . ሁሉንም እንደተፈለገ እየተጨፈለቀ አይደለም፡፡ ‹‹ የጥበብ መጀመሪያ እግዚሐብሔርን መፍራት ነው ›› ይላል ዳዊት በመዝሙሩ (111 ፤ 10) የውስጥ ችግር ካልሆነ አድገዋል የምንላቸው አብዛኛዎቹ ሀገራት በሙሉ ለሐይማኖት አባቶቻቸው እንዲሁም ለእምነት ተቋሞቻቸው ክብርና ቦታ ይሰጣሉ፡፡ ( የሚሰጡበት መንገድ ትክክልም ይሁን አይሁን) በተቃራኒው እኛ ደግሞ ማጥፋት እየጀመርን ነው፡፡ ጥበብ ወይም እድገት መነሻው እግዚአብሔር ነው፡፡ እሱን ለሚወዱና ለሚያከብሩ ደግሞ አክብሮት ሊኖረን ይገባል፡፡

‹‹ . . .ክፉ ነገር ሀገራችንንም አያገኛትም፡፡
ነፋስ እንዳይገባባችሁ በያላችሁበት ጠብቁ፡፡ ወንድሜ ወንድሜ
ተባባሉ. . . ›› አፄ ሚኒሊክ

የእውነት ኢትዮጵያችን የተደራጀ ጦር ቢኖራት፣ የእህል ጎተራዎቿ ቢሞሉ፣ የጥናት ማዕከላት ላይብረሪና ዩኒቨርስቲዎች ቢገነቡ፣ ሆስፒታሎች በየአካባቢው ቢኖሩ፣ መንገዶች ቢስፋፉ ደስታው የሁሉም ነው፡፡ መንግስትም ይህ አስፈላጊ እንደሆነ እንደሚያውቅ እገምታለሁ ይህንን ሊያሟላ እንደሚጥርም ግልፅ ነው፡፡ በዚህ ጥረት መካከል ግን ‹‹ ይህ ለምን ይሆናል›› . . . ‹‹ አረ. . አረ. . .›› ‹‹ ለማን አቤት እንበል›› የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ ይሰማል፡፡ ቅሬታዎች እየበዙ ነው፡፡ ህዝብን መስማት ደግሞ ትልቅነት እንጂ ፈሪ መሆን አይደለም፡፡ ምንም ይሁን ምን ህዝብ ከመንግስት ይበልጣል፡፡ ህዝብ አዋቂ ነው፤ መንግስትም ከህዝብ መውጣትና መምሰል አለበት፡፡ ገና ሳናድግ ልማት ላይ ካልተስማማን ሁሉም ነገር ታጥቦ ጭቃ ነው የሚሆነው፡፡ ለሁሉም ክብር ይሰጥ በተለይ ለዕምነት ተቋማት፡፡

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org